دار زايد للثقافة الإسلامية
Zayed House For Islamic Culture

# ማኅበራዊ መቻቻል

ፀሐፊ ፡ ሻይካ ናስር አል ካርቢ

zhic.uae @zhic_uae zhic_uae zhic
800 555 اتصل على JUST CALL
P.O Box: 16090, Al Ain, U.A.E
www.zhic.ae contact@abudhabi.ae

ዳር زايد للثقافة الإسلامية
Zayed House For Islamic Culture

ማኅበራዊ መቻቻል በአጠቃላይ መልካም ከሆኑና በማኅበረሰቡ ውስጥ የያንዳንዱን ግለሰብ ማንነት ሊያሳምሩ ከሚችሉ እሴቶችና ማኅበራዊ ተግባራት ጋር የሚጣጣም ነው፡፡ ሁሉንም በሚበቃ መልኩ ለሁሉም ሰው አጠቃላይ የሆነ ደህንነትና ማኅበራዊ ዋስትናን ይሰጣል፤ ለያንዳንዱ ግለሰብም መብቱንና ለወደፊት ሕይወቱ ጭምር ዋስትና ይሰጠዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ማኅበራዊ መቻቻል የተከበረ ሕይወት ለመኖር፣ ከሌሎች አንፃርም መልካም ሥነምግባር ለማንፀባረቅና ሌሎችን ለማክበር፣ አክብሮት ለመስጠትና ለማኅበረሰቡ የሚሰጠውን አገልግሎት ሁሉ ዋጋ ለመስጠት ምርጥ የሆነ መለያ ነው፡፡ መጪውን ትውልድ ለማነፅ ለያንዳንዱ ሰውም ሰላማዊና ምቹ የሆነ ከባቢን ይፈጥራል፡፡

ማኅበራዊ መቻቻል ከሚይዛቸው ነገሮች መካከል ልጆችን በመልካም ሥነምግባር ማሳደግ፣ በመቻቻል ባህሪ ላይ ማሳደግና በተለያዩ ነገሮች ውስጥ መተግበርን ያጠቃልላል፡፡ ይህ እነፃ ደግሞ አስተማሪ የሆነን ከባቢ ይፈጥራል፡፡ የትምህርት መርሃ ግብሮችም የመቻቻልን አስፈላጊነትና ለግለሰብም ሆነ ለማኅበረሰቡ የግድ እንደሆነ ለልጆች ማስተማር ይገባቸዋል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ይህን ግንዛቤ እና እሴትን ለመተግበር የሚያግዙ ተግባራዊ ፕሮግራሞችና መርሃ ግብሮች መኖር አለባቸው፡፡ ይህም የዛሬዎቹ ሕፃናት ወደፊት ከሌሎች ጋር በሚኖራቸው መስተጋብሮችና ድርጊቶቻቸው ውስጥ ለመተግበር ያስችላቸዋል፡፡

የመቻቻልን እሴት በተለያዩ የማኅበረሰቡ ክፍሎች ውስጥ መከባበርን ለማስገኘት፣ አመለካከቶች፣ አስተሳሰቦችን እና የተለያዩ ልምዶችን ለማስረጽ የሚያግዝ ስለመሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ በዚህም የተነሳ እያንዳንዱ ግለሰብ የመከበር ዕድል ያገኛል፡፡ ምክንያቱም የማኅበራዊ መቻቻል ትርጉሙ ከግለሰብ እና ማኅበረሰብ እነፃ ውጤት ከሆነው ከሥነምግባር የተያያዘ ነውና፡፡ እዚህ ላይ የሰው ልጅ ማኅበረሰብ በግለሰብ ደረጃ ጭምር ከሥልጣኔ ብዛህነት የሚያገጥማቸውን ውጤቶች ማየት ይቻላል፡፡ ይህም ከማኅበራዊ ትስስር ጥሪ አንፃር ተፃራሪ የሆነውን ማንኛውንም ባህሪ ለማስተካከልና ለማረም ይህን እሴት ማስረጽ የግድ መሆኑን አመላካች ነው፡፡

በአባላቱ መካከል የመቻቻልን እሴት ለማስገንዘብና ለማስረጽ የሚሰራ ማንኛውም ማኅበረሰብ ማምረትና ማሳመርን እንዲሁም በአባላቱ መካከል መተባበርን ብቻ የሚያውቅ፤ የተከበረና የተረጋጋ ሕይወት የሚመራ ማኅበረሰብ ይሆናል፡፡ ከፍተኛ የሆነ የሥነልቦና እና የማኅበራዊ ደህንነት ዋስትና ያገኛልም፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ መቻቻል አዲስ ማኅበረሰብ ለመገንባት ዋንኛ መሣርያ ይሆናል፡፡ ዓላማ እንዲሁም ወደ ግብ ማድረሻ መሣርያም ነው፡፡ ወደርሱ መድረስ ማኅበረሰቡን ከፍ ያደርጋል፡፡ በሱም አማካይነት እያንዳንዱ ግለሰብ የተከበረ ሕይወት ያገኛል፡፡ በዚህም የተነሳ የግለሰብም ሆነ የማኅበረሰብ ደህንነት የተረጋገጠና የተሟላ ይሆናል፡፡